በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ሱሰኞች - ቤተ ክርስቲያንና - ቤተሰብ
# ክፍል 2

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf : [www.zeorthodox.org](www.zeorthodox.org)

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ሰኔ ፳፮ ቀን ፳፻፰ ዓ.ም.**

# ሱሰኞች - ቤተ ክርስቲያንና - ቤተሰብ - ክፍል 2

## ይመለከተኛል እንበል…

4. ***ሱሰኝነት ከተሳሳተ አመለካከትና እምነት ይመነጫል… ስለ ነጻነት ያለን የተሳሳተ አስተሳሰብ አንዱ ነው…***

- *መታዘዝን እንደ ደካማነት መቁጠር ታላቅ ስህተት ነው፡፡ ወላጆቻችን፣ መምህራን እና የቤ/ክ አባቶች ትእዛዝ አስተላልፈው ጭፍን ታዛዥነትን ሲጠብቁብን ተሰላችተን ከመታዘዝ ልንቆጠብ እንችላለን፤ ታዲያ ይህ አጋጣሚ በቀላሉ ሰዎችን የሱስ ‹‹ባልንጀራ›› ወደ መሆን ያደርሳቸዋል፡፡*
- *ዛሬ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያጠናቅቁ በርካታ ተማሪዎች ለፓርቲ - ሌሊቱን አብሮ የማሳለፋቸው ልምድ እየተስፋፋ የሚገኝ ነው፡፡ ታዲያ አንድ ልጅ ወላጆቹን ለዚሁ ጉዳይ ፈቃድ እንዲሰጡት ጥያቄውን ሲያቀርብላቸው ብዙም ትእዛዝ መቀበል እንደማይወድ አስቀድመው ስለሚያውቁ በቤተ ክርስቲያን (በሰንበት ት/ቤት) የሚያስተምረውን መምህር እንዲያማክር ይነግሩታል፤ መምህሩም እኔ ልመልስልህ ባልችልም ልጄ ባለፈው ዓመት በተመሳሳይ ሂደት ስላለፈ እርሱን አናገረው ይሉታል፡፡ ሁለቱም ሲነጋገሩ የመምህሩ ልጅ እኩያው ለርሱ መልካም ባልሆኑ ምግባሩንም ሊያበላሹ በሚችሉ ነገሮች ተሳትፎ ከማድረግ እንዲቆጠብ ወደ ፓርቲው እንዳይሄድ ሲነግረው ሙሉ ለሙሉ ተስማምቶ ቀረ፤ ይህንም ስምምነቱን ጭፍን ትእዛዝ ተሰጥቶኛል ብሎ ሳያስብ መቀበሉን አረጋገጠ፡፡ መምህሩም ዝም ብሎ ከማዘዝ ይልቅ በዚህም ዘዴ በመጠቀም በልጁ ዘንድ ታማኝነትን ለማትረፍ እንደበቁ ልብ አላችሁ!፡፡*
- *ጌታችን በፈቃዱ ለአባቱ ፈቃድ በመታዘዙ ያስተማረን ደካማነትን ሳይሆን ፍቅርን ነው፤ መታዘዙ መለኮታዊ ድልን አቀዳጀ እንጂ ከአባቱ ጋር ያለውን አንድነት አላጠፋውም፡፡*
- *አንዲት እናት አጥፊ ስለሆነውና ምክርዋን ስለማይቀበለው ልጅዋ ጉዳይ ምክር ለመጠየቅ ወደ ንስሐ አባቷ ትሄዳለች፡፡ ለካህኑም ልጄ ስመክረው ‹‹ምክርሽ ትክክል ቢሆንም የማልቀበለው ደካማ ሰው መሆን ስለማልፈልግ ነው›› አለኝ ብላ ነገረቻቸው፡፡ ካህኑም ‹‹ሆን ብለሽ በልጅሽ ፊት ስህተት ሥሪ፤ ካረመሽም ያለሽን ተከትለሽ*

# ሱሰኞች - ቤተ ክርስቲያንና - ቤተሰብ - ክፍል 2

4. ***<u>ሱሰኝነት ከተሳሳተ አመለካከትና እምነት ይመነጫል… ስለ ነጻነት ያለን የተሳሳተ አስተሳሰብ አንዱ ነው…</u>***

- ስህተቱን አርሚ፡፡ በመቀጠልም ‘አንተ ልጄ ስትሆን ምክርህን ተቀብዬ በተግባር ማሳየቴ ደካማነት ነውን? አይደለም’ ብለሽ አስረጅው፡፡ ልጁም መታዘዝ ደካማነት ወይም ብልሹ ምግባር ማለት እንዳልሆነ ይረዳል፡፡ ትእዛዝ ከጋራ ፍቅርና ሰላማዊ ከሆነ ውይይት/ምክክር መመንጨት ይገባዋል እንጂ የግድ ከታላላቆች ለወጣቶች የሚተላለፍ ብቻ መሆን የለበትም፡፡›› ብለው ቢመክሯት እርስዋም ተቀብላ ተጠቀመችበት፡፡
- ሱሰኝነት ሃይማኖት ያረጀ፣ ጊዜ ያለፈበትና መጥፎ ጫና ፈጣሪ እንደሆነ ከማሰብ ይመነጫል፡፡ ሱሰኞች ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን ግትርና ምሕረት-የለሽ አድርገው ያስባሉ፡፡ ‹‹ልጄ ሆይ፥ ኃጢአተኞች ቢያባብሉህ እሺ አትበል፡፡›› ***<u>ምሳ 1፡10፡፡</u>***
- ስለዚህ መንፈሳዊ መሪዎች (መምህራንም) በንግግራቸውና በድርጊታቸው ሃይማኖትን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝና ወደ ደስታ የሚያደርስ መንገድ ፣ በአባታችን ፍቅር ደስ የምንሰኝበት ዘላለማዊ በረከት፣ ከክርስቶስ ስጦታ ከመንፈስ ቅዱስ ሀብታት ተሳትፎ ማድረግ፣ ክፉውን ዓለም በማሸነፍ ወደ ታላቁ ከፍታ ወደ መንፈሳዊነት መድረስ፣ በእግዚአብሔር እቅፍ እስክንሆን ድረስ ከድል ወደ ድል የሚያሻግር ጎዳና ማለት እንደሆነ ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ‹‹ነገር ግን ተናገር ዝምም አትበል፤ በዚህ ከተማ ብዙ ሕዝብ አሉኝና አለው፡፡›› ***<u>የሐዋ 18፡10</u>***
- ቤ/ክ ኃጥአንን ይልቁንም ሱሰኞችን የማታቀርብ የምትንቃቸውና የምታቃልላቸው አድርጎ በሚመለከት ሥዕል የተረዷት አንዳንዶች ይኖራሉ፡፡ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ቤ/ክ ፍርድ ቤት ሳትሆን ሐኪም ቤት ናት ሲል ባስተላለፈው መልእክት መሠረት ዘወትር በቤተ ክርስቲያን የሚደረገውን እንዲረዱ እናስታውሳቸዋለን፤ ሱሰኞች ከሱስ ባርነት በቤተ ክርስቲያን ሰማይነት ይላቀቁባታልና፡፡
- በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሱሰኞች ራሳቸውን የሱስ እስረኞች አድርገው ይቀበላሉ፡፡ ከሱስ መላቀቅ ቢፈልጉም ቁስለኞች ናቸውና ዝለት ይሰማቸዋል ወይም ጉልበታቸው ይከዳቸዋል፡፡ ታዲያ በዚህ ሕይወት የሚኖሩ ሁሉ በሚያፈቅራቸው እውነተኛ መንፈስ መፈወስ ያስፈልጋቸዋል፤ ያም መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡

# ሱሰኞች - ቤተ ክርስቲያንና - ቤተሰብ - ክፍል 2

4. ***ሱሰኝነት ከተሳሳተ አመለካከትና እምነት ይመነጫል... ስለ ነጻነት ያለን የተሳሳተ አስተሳሰብ አንዱ ነው...***

- በአንድ ወቅት አንዲት ሴት ወደ ካህኑ በመሄድ ‹‹ነፍሴን አጥፍቻታለሁ፡፡›› ትላቸዋለች፡፡ ካህኑም ‹‹ለምን?›› ብለው ሲጠይቋት ‹‹ምክንያቱ እርስዎ ነዎት›› ብላ መለሰችላቸው፡፡ ካህኑ ቢደነግጡም ራሳቸውን በመግዛት ‹‹ምን አደረግሁ›› ብለው ጠየቋት፤ እርሷም ‹‹ዘወትር ወደ ቤተ ክርስቲያን ስመጣ ስለ ኃጢአት አስፈሪነትና መራርነት ሲናገሩ እሰማዎታለሁ፡፡ እኔም የኃጢአት ባሪያ ስለሆንኩ ምን ላድርግ?›› ብላ መለሰችላቸው፡፡ ካህኑም ከፍተቱን በመረዳት ‹‹ኢየሱስ ክርስቶስ በበዛ ፍቅር የሚወደንና የሚራራልን ኃጢአተኞችንም በተዘረጋ እጁ የሚቀበላቸው ደግ አምላክ ነው፡፡›› በማለት ስለ ንስሐና ንስሐን ስለሚቀበለው አምላካችን ገንቢ በሆነ መንገድ ቢያስረዷት ተረጋግታ ለመመለስ ንስሐ ገብታም በርጋታ ለመኖር በቅታለች፡፡
- በኃጢአታቸው ላይ ትኩረት አድርገን በባርነት የሚኖሩበትን ሱሰኝነቱን አቆሽሸን ካቀረብን የሱሰኞች ነፍሳቸው ትጠፋለች፡፡
- ስለዚህ ገነትን፣ ከዘላለማዊት ርስት መካፈልን፣ በአዲሱ ሕይወት በመንግሥተ ሰማያት ደስ መሰኘትን አስመልክቶ ጥልቅ ትኩረት በመስጠት ያሳየንን ያስተማረንን ጌታችንን ምሳሌነት ተከትለን ለሌሎች ተስፋን መፈንጠቅና ማሳየት ይጠበቅብናል፤ ይህንም በጎ ጎዳና በማሳየታችን በደካማነት ዝለው ለወደቁት ሁሉ የተስፋን መንፈስ እንፈነጥቅላቸዋለንና፡፡ ‹‹ኢየሱስም ወጥቶ ብዙ ሕዝብ አየና እረኛ እንደሌላቸው በጎች ስለ ነበሩ አዘነላቸው፥ ብዙም ነገር ያስተምራቸው ጀመር።›› ***ማር 6፡34፡፡***
- - በአንድ በኩል በቤ/ክ ወይም በሚያምኑ መካከል በሌላ በኩል በቤት ወይም በሥራ ገበታችን ከማያምኑት መካከል ሆነን ባልተረዳ ነገር መንታ ሕይወትን መምራታችን በእውነት የሚኖሩበትንም የሚያስመስሉ አድርገን እንድናስብ መገፋፋቱ እውነተኛ ሰው የለም የሚል ድምዳሜ በመያዝ ወደ ሱሰኝነትና አጥፊ ሕይወት እንድናመራ ያደርጋል፡፡
- ሌላኛው የተሳሳተ አመለካከት ያልተማሩ አንዳንደች እጽ ፍትወትን የሚያነሳሳ አድርገው ማቅረባቸው አዳዲስ ሙሽሮች ፈቃደ ሥጋን የሚፈጽሙበት ጉልበት ለማግኘት አስፈላጊ መሣሪያ እንደሆነ እንዲያስቡ መገፋፋቱ ነው፡፡

# ሱሰኞች - ቤተ ክርስቲያንና - ቤተሰብ - ክፍል 2

## ይመለከተኛል እንበል…

5. ***ሱስና ራስን ከመጥላት ይመነጫልና***

- *ሥነ ልቦናዊ ችግሮች በአንደኛውና በሦስተኛው ዓለም በተመሳሳይነት አድገዋል፡፡ ከዚህ ችግር ለመገላገልም መድኃኒቶች ጊዜያዊ መጠለያ እየሰጡ ይገኛሉ፤ ስለዚህም ሱሰኝነትን ማከም በርካታ ሥነ ልቦናዊ ጥንቃቄን ይጠይቃል፡፡ ዘመናዊው ሰው ይህን የተዘበራረቀ ዓለም ልበ-ሰፊ በመሆን በአርቆ አሳቢነትና ባለመፍራት የሰውን ወገን በሚወደው በእግዚአብሔር ክንድ በመታመን እንዲጋፈጠው ይጠበቅበታል፡፡ **ዮሐ 16፡33፡፡***
- *ዓይንን ገልጦ እጆቹን ዘርግቶ ሰላሙን ሊሰጠን የቀረበውን ክርስቶስን መቀበል፣ ብሎም በዓለም በሚኖረን ፈተና ሁሉ እርሱንና መስቀሉን ተሸክመን በእምነት መንፈስ ሆነን ከተራመድን በአውደ ውጊያው ሁሉ ‹‹ዓለሙን አሸንፈዋለሁ!›› ማለት እንችላለን፡፡ ቅዱሳኑም በዚህ ዓለም መሻት ሳይወሰዱ ይህን ዓለም ያሸነፉት በርሱ ነውና፡፡*

6. ***የአቻ ጓደኞች ግፊት የሱሰኝነት ምክንያት ሊሆን ይችላልና***

- *ሳይንቲስቶች በርካታ ሱሰኞች ወደ ሱሰኝነት የተቀላቀሉት በአቻ ጓደኞቻቸው ግፊት እንደሆነ አትኩሮት ሰጥተው ይናገራሉ፡፡ በርግጥም የሃይማኖትና የማኅበረሰብ መሪዎች ለዚህ ግፊት ወይም ጫና መፈጠር ተጠያቂዎች ናቸው፡፡*
- *በቤተ ክርስቲያን ሥልጣን የተሰጣቸው ሰዎች ከልብ በመነጨ መሠረት ላይ የታነጸውን፣ ሰላማዊ ምክክር ያለበትን፣ የተከበረ ቤተሰባዊ አመለካከት የነገሠበትን የወዳጅነት መንፈስ እየለቀቁ/እየናቁ ሲሄዱ ሰዎች ስለ ወላጆች፣ መምህራን፣ ካህናት፣ መንፈሳዊና ዓለማዊ መሪዎች ወይም ስለ ሰዎችም ያላቸው አመለካከት እስከ መጨረሻው የማይታከም ነቀርሳ ይይዘዋል፡፡*
- *እነዚህም አስቀድሞ ይህን የተዛባ አመለካከት የራሳቸው መጠለያና መጠጊያ አድርገው በቆዩ ጓደኞቻቸው ተጽእኖ ሥር ይወድቃሉ፤ ያለፈቃዳቸውም ስለሄዱ ሱሰኞቹ እንደ ወደዱት አድርገው አቅልጠው መልሰው ይሰሯቸዋል፡፡*

# ሱሰኞች - ቤተ ክርስቲያንና - ቤተሰብ - ክፍል 2

## ይመለከተኛል እንበል…

7. ***ሱስና በውጫዊ ተጽእኖ ሊከሰት ይችላልና***

- አንድን ሰው ወደ ሱሰንነት ለመምራት ውጫዊ ተጽእኖዎች ያላቸው ሚናም ሊረሳ የማይገባው ነው። እጽ በማዘዋወር ትርፋቸውን ለማሳደግ ከሚሹት ጀምሮ፣ ፖለቲካዊ ትርፍ ለማትረፍ ሲሉ አንዳንድ አገሮች በሌሎች አገሮች ላይ የሚሠሩት ሥራም ከዚህ አንጻር ሊዘነጋ የማይችል ተጽእና ነው። በላቲን አሜሪካ አገሮች የቡና ዋጋን መውደቅ ተከትሎ ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻቸውን ለመፍታትና አገራዊ ዓመታዊ ገቢያቸውን ለማሳደግ የአደንዛ ዕፅ ምርትን ማሳደግን እንደ መፍትሔ እንዲወስዱት መገደዳቸው ከውጫዊ ተጽእኖዎች የሚቆጠር ነው። በነዚህም ግፊቶች የተነሣ ምእመናችንም ሆነ ሕዝቡ አደንዛዥ እጾች ስለሚያስከትሉት አደጋና ስለሚፈጥሩት ተጽእኖ ማስተማር ይጠበቅብናል።

8. ***ልሞክረው ከማለት የተነሳ ወደ ሱስ መዘፈቅ ይኖራልና***

- አንዳንድ ሰዎች አደንዛዥ እጾችን ልሞክር በሚል ፍላጎት ብቻ ገብተውበት በሱሰኝነት ተዘፍቀው ይቀራሉ፤ እንዲህ ያሉም ሰዎች በወጣትነታቸው ስለ አደንዛዥ እጽም ሆነ ስለ ሱስ በቂ ትምህርት ያላገኙ ናቸው።
- ስለዚህም ያሉበት ሁኔታ ምንም ይሁን ምን ሰዎች መረጃን (እውነታዎችን) ከጓደኞቻቸውና ከሙከራቸው እንዲያገኙ ከመተው ይልቅ ታማኝ ከሆነችው ምንጭ ከቤ/ክ ለሰዎች ማድረስ ይጠበቅብናል። ***ምሳ 22፡6፡፡***

9. ***ሱስና በራስ መተማመን***

- ዝቅ ያለ በራስ የመተማመን ስሜትና የሕይወት ቀውስ (ጫና) ውስጣቸው ካለው ስሜት ለማምለጥ የሚሞክሩ ሰዎችን ወደ ሱሰኝነት ተገፍተው እንዲገቡ ያደርጋቸዋል።
- በሚፈልጉት ጊዜ ሱስን ለመተው የሚያስቻላቸው ጉልበት እንዳላቸው ለማሳየት ሲሉ የሚያጤሱ ወይም እጽን በመድኃኒት መልክ የሚወስዱ ሰዎች ይህን የመሰለው ከልክ ያለፈ በራስ መተማመን ስሜት የማይላቀቁት እስረኞች እስኪሆኑ ድረስ የአደንዛዥ እጽ ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል።

# ሱሰኞች - ቤተ ክርስቲያንና - ቤተሰብ - ክፍል 2

## 9. *ሱስና በራስ መተማመን…*

- ይህም አካሄድ አዲሱ ትውልድ በእግዚአብሔር ተደግፎ እንዲኖር የሚያደርገውን ትምህርት እንድናስተምረው፣ ስለተሰጣቸውም ጸጋና ሀብት እንድናስገነዝባቸውና የራሳቸውን ችግር ለመፍታት ግድየለሽና ተስፋ-ቢስ ከመሆን እንዲቆጠቡ ልናስታውሳቸው እንደሚገባ የሚያሳስበን ነው፡፡
- ይህንም ለማድረግ ከመፍራት ይልቅ እንዳንወድቅ ጥንቃቄ ከማድረግ ጋር እግዚአብሔር ስለሚያደርግልን ጥበቃ በመረዳት በእምነት ልንራመድ ይገባናል፡፡

**የሐሳብ ሱሰኝነት**

- ሱሰንነት የአልኮል፣ የእጽ፣ የሲጋራ ወዘተ ብቻ ሳይሆን የሐሳብ ሱሰኝነትንም ያካትታል፡፡ ይህም ያለ ውይይት በሌላ መንገድ የሚያስቡ ሰዎችን በመጥላት፣ በማስጠላት በሌሎች ላይ የሚጫን ሐሳብ ሱሰኝነትን ወይም
- በአንድ ሰው ሱሰኞ መሆንን የተመለከተ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የታወቂ ሰዎችን ሞት ተከትሎ ራሳቸውን የሚያጠፉ ሰዎችን ተመልክተናል፤ እነዚህም በሰዎቹ ሱሰኝነት የተያዙ ናቸው፡፡
- ይህን ዓይነት ሱሰኝነት በሃይማኖት በሚኖሩትም መካከል ይከሰታል፡፡ በሃይማኖታቸው መልካምነት የሚኖሩ ሰዎችን መልካምነት ብቻ እየወሰዱ ራስን ከመጥቀም ይልቅ እንደ ጣዖት የሆነባቸውን ደካማ ስብእናቸውን ሁሉ እየወሰዱ በሰዎቹ ሱስ ራሳቸውን የጠመዱ አንዳንድ ሰዎችም ይገኛሉ፡፡ የምናደንቃቸውን መምሰል መልካም ቢሆንም ነፍሳችንን ሊያንጻት የሚችለው ግን እግዚአብሔር እንደሆነ ልብ በማለት፤ ሌሎች ሰዎችንም እንደ እግዚአብሔር ከመቁጠር መቆጠብ ከኦርቶዶክሳውያን ሁሉ የሚጠበቅ ነው፡፡

**የልማድና የባሕል ሱሰኝነት (ባርነት)**

- የሙዚቃ… ሱሰኞች ‹‹ነጻነትና ደስታ›› እንደሚያገኙበት ቢቆጥሩም ነፍሳቸውን እያጡበት መሆኑን ይዘነጉታል፡፡
- ‹‹ እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ። ›› ***ዮሐ 8:36***፣ ‹‹ ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋልና፤ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይስጥ፥ ነገር ግን በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ። ›› ***ገላ 5:13፡፡***

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org